## የ ጥቁሮች የታሪክ ወር /Black History Month/ በኢትዮጵያ ኤምባሲ ተከበረ

በዩናይትድ ስቴትስ በየካቲት ወር በተለያዩ ዝግጅቶች ወሩን ሙሉ የሚከበረው የጥቁሮች የታሪክ ወር (Black History Month) ምክንያት በማድረግ በአፍሪካና በአፍሪካ አሜሪካዊያን መካከል ላለው የጠበቀ ትስስር ተምሳሌት የሆኑና ልዩ ሚና የሚጫወቱ አፍሪካን አሜሪካውያን ታዋቂ ግለሰቦች ወይም ተቋማትን አስተዋጽኦ ለመዘከር የሚያስችል ዝግጅት እ.ኤ.አ. የካቲት 25 ቀን 2008 ምሽት ዋሽንግተን ዲሲ በሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ ተካሂዷል:: በዚሁ መሠረት የዘንድሮው የጥቁሮች የታሪክ ወር ከኢትዮጵያ ጋር የጠበቀ ትስስር ያለውንና ሁለት መቶኛ አመቱን ለማክበር በዝግጅት ላይ ያለውን የአቢሲኒያ ባፕቲስት ቤተክርስቲያን እውቅና በመስጠት በኤምባሲው በታላቅ ድምቀት ተከብሯል:: በዚህ በዓል ከ350 በላይ የሚሆኑ የዩኤስ ስቴት ዲፓርትመንት፣ የዲፌንስ ዲፓርትመንትና ፔንታገን በየደረጃው ያሉ ኃላፊዎች፣ ኮንግረሽናል ስታፈርስ፣ የዲስ መስተዳድር ሃላፊዎች፣ የታዋቂ አፍሪካን አሜሪካውያን ተቋማት መሪዎች፣ ታዋቂ ግለሰቦች፣ ፣ የአፍሪካና ካረቢያን አምባሳደሮችና ተወካዮች፣ ከአፍሪካን አሜሪካዉያን ጋር ትስስር ያላቸው ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን ተገኝተዋል:: እንዲሁም ሬቨረንድ ካልቪን በትስ እና በቅርቡ በአቢስኒያን ባፕቲስት ቤተክርስቲያን አስተባባሪት ከኒውዮርክ ወደ ኢትዮጵያ ከተጓዙት ጥቁር አሜሪካውያን መካከል 60 የሚሆኑት በዝግጅቱ ላይ ተገኝተዋል:: በዩኤስ ስቴት ዲፓርትመንት የአፍሪካ ጉዳይ ረዳት ሴክሬታሪ ሚስ ጄንዳይ ፍሬዘር በዝግጅቱ የተገኙ ሲሆን የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ከንቲባ ሚስተር አንድሪያን ፌንቲ በበዓሉ ለመገኘት አለመቻላቸውን በመግለጽ የጥቁሮች የታሪክ ወር በማስመልከት በኤምባሲው ልዩ ክብር የተሰጠውን የአቢሲኒያን ባፕቲስት ቤተክርስቲያንና ለኢትዮጵያ ኤምባሲ መልካም ምኞታቸውን በመግለጽ ስቴትመንት ያወጡ ሲሆን ይኸው በበዓሉ ሥነሥርዓት ላይ በንባብ ተሰምቷል:: በዝግጅቱ ክቡር አምባሳደር ሣሙኤል አሰፋ፣ ሬቨረንድ ካልቪን በትስ ፣ ፕሮፌሰር ኤፍሬም ይስሐቅ፣ ፕሮፌሰር አቢይ ፎርድ እና ፕሮፌሰር አለም ሀብቱ ንግግር አሰምተዋል::

አምባሳደር ሣሙኤል አሰፋ ባደረጉት ንግግር የጥቁሮች የታሪክ ወር የአፍሪካዊያንና አፍሪካን አሜሪካዊያን የጋራ ማንነት ለመዘከርና ዘላቂ የሆነ መተሳሰብ ለማጎልበት የሚያስችል መሆኑን ገልጸዋል:: ከዚህ አንፃር ኤምባሲያቸው በአፍሪካዊያንና በአፍሪካን አሜሪካዊያን መካከል ላለው ልዩ ትስስር ተምሳሌት ለሚሆን ግለሰብ ወይም ተቋም እውቅና በመስጠትና በመዘከር የጥቁሮች የታሪክ ወር በየአመቱ እንደሚያከብር ገልጸዋል:: በዘንድሮ አመት በሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት ስር የሰደደና

አንፀባራቂ ታሪክ ያለውን የአቢሲኒያን ባፕቲስት ቤተክርስቲያን የመጀመሪያው እውቅና የተሰጠው ተቋም መሆኑን በመግለጽ ስለቤተክርስቲያኗ አመሠራረት በተለይም ከኢትዮጵያ ጋር ስላላት ትስስር አብራርተዋል።

ፕሮፌሰር ኤፍሬም ይስሐቅ በበኩላቸው የጥቁሮች የታሪክ ወር ከአፍሪካዉያን እይታ አንፃር በመተርጐም በ1960ዎች በትምህርትና በተለያዩ ምክንያት ወደ ዩናይትድ ስቴትስ የተሰደዱት ኢትዮጵያውያን ያጋጠማቸውን ሁኔታ በተመለከተ ከራሳቸው ልምድ አንፃር አቅርበዋል።

የሀዋርድ ዩኒቨርስቲ ፕሮፌሰር የሆኑት ዶ/ር አቢይ ፎርድ በበኩላቸው በአፍሪካዊያንና በአፍሪካ-አሜሪካዊያን መካከል ያለው የደም ትስስር ከራሳቸው ተሞክሮ አንፃር ያስረዱ ሲሆን በአድዋ ጦርነት ጊዜ አፍሪካን አሜሪካዊያን የተጫወቱትን ሚናና ኮማርከስ ጋርቬይ እንቅስቃሴ ጋር በማዛመድ ተናግረዋል።

ፕሮፌሰር አለም ሀብቱ /በኒውዮርክ ሲቲ ዩኒቨርስቲ የሶሽሎጂ ፕሮፌሰር / በ1960ዎችና በ1970ዎች በአሜሪካ የተካሄደው የሲቪል መብቶች እንቅስቃሴ በኢትዮጵያውያን ምሁራን ላይ ያሳደረው ተጽእኖና በወቅቱ በአሜሪካ ስለነበረው የኢትዮጵያውያን የተማሪዎች እንቅስቃሴ በተመለከተ ንግግር አድርገዋል።

የዕለቱ የክቡር እንግዳ ሬንቨረንድ ካልቪን በትስ ባደረጉት ንግግር የአቢሲኒያ ባፕ ቲስት ቤተክርስቲያን ሁለት መቶኛ አመቱን በዓል በሚያከብርበት ወቅት በኢትዮጵያ ኤምባሲ ለተሰጠው እውቅናና ክብር አድናቆታቸውን በመግለጽ የቤተክርስቲያኑ ስም ኢትዮጵያን የሚወክል እንደመሆኑ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ያለውን ትስስር ለማጉልበት እንደሚጥሩ ገልጸዋል። በሳቸው የተመራው የቤተክርስቲያኑ የልዑካን ቡድን የኢትዮጵያን ሚሊኒየም በኢትዮጵያ ተገኝቶ ማክበሩና በኢትዮጵያ ለተደረገላቸው አቀባበል የተሰማቸውን ስሜት በማስታወስ ኢትዮጵያን በጤና፣ ኤች.አ.ይ.ቪ/ኤድስ በመከላከልና በኢኮኖሚ ለመርዳት ቤተክርስቲያኗ የበኩሏን አስተዋጽኦ ለማድረግ እንደምትንቀሳቀስ ገልጸዋል። በዚሁ ጊዜ ለአንድ የኢትዮጵያ ትምህርት ቤት የሚሰጥ መጽሐፍና እንዲሁም በኢትዮጵያ ጉብኝታቸው ወቅት ላገኙዋቸው ወጣቶች የሚሰጥ የስፖርት ትጥቅ በስጦታ አበርክተዋል።

በበዓሉ በአሜሪካ የጥቁር ሲቪል መብቶች ንቅናቄ ላይ ያተኮረ የሰዕል ኤግዚቢሽን አርቲስት ቴሲል ዳዊት በተባለ ኢትዮጵያዊ አርቲስት የቀረበ ሲሆን የአቢሲንያን ባፕ

ቲስት ቤተክርስቲያን አመጣጥና አስተዋጽኦ፣ የአድዋ ጦርነትና የጥቁሮች ተሳትፎ፣ በአሜሪካ በ1960ዎች የነበረው የጥቁሮች የሲቪል መብቶች ንቅናቄ አስተሳስሮ የሚያሳይ ስዕል በክቡር አምባሳደር ሳሙኤል አሰፋ ለአቢሲኒያን ባፕቲስት ቤተክርስትያን ተበርክቷል።

በበዓሉ ላይ የአቢሲኒያን ባፕቲስት ቤተክርስቲያን የሶሎ ሙዚቃ ያቀረበ ሲሆን፣ የኢትዮጵያ ባህላዊ ምግብ እና የአፍሪካን አሜሪካዊያን ምግብ ቀርቧል። በዝግጅቱ በርካታ በዋሽንግተን ተቀማጭ የሆኑ የአፍሪካ አሜሪካዊያንና ሌሎች ሚዲያዎች ተገኝተዋል።

የኢትዮጵያ ኤምባሲ
ዋሽንግተን ዲሲ